# ብርቱ እናት!
# ብርቱካን ናት!

**ብርቱካን የአመቱ ሰው ተብላ በቫንኮቨር ካናዳ በተሸለመችበት ወቅት የቀረበ ጽሁፍ**

(ከመላኩ ፀጋዬ መኮንን)

የእኔ እናት ወያኔዎች አዲስ አበባን የተቆጣጠሩ እለት የደረሰባትን መጨነቅና መጠበብ ብሎም የሕሊና የአካል መነሳቆል እኔው እራሴ ቆሜ ያየሁት እውነታ የሽምቅ ተዋጊዎቹ አዲስ አበባ መግባታቸውን ስትሰማ ከየት እንደመጣ ያልታወቀ የረጋ ደም በአፏ ቡልቅ ቡልቅ ብሎ ወጣ። ቀደም ባሉት አመታት ሁለቱ ወንድሞቼ ከገጠር ደብረታቦር ከተማ ለገበያ ሂደው በደርግ ካድሬዎች ለስድስት ወራት ታስረው እማማ ስንቅ በማቀበልና ከዛሬ ነገ ተገደሉ የሚለውን ወሬ ለመስማት ቀን እየቆጠረች ሳለ አጋጣሚ ሆኖ ከስር ተፈተው ወደ ግብርና ሥራቸው ተመለሱ። ታዲያ የዚህ ሁሉ መከራ መነሻው የአንድ ወቅት ብቻ ሳይሆን ከአብዮቱ መባቻ ጀምሮ በሀገሪቱ በደረሰው የእርስ በእርስ ፍጅት ያስከተለው ሰቆቃ ጭንቀት አካል ነው።

እናቶች ልጆጃቸው እንደወጡ ሳይመለሱ ቀሩባቸው፤ከመኖሪያቸው ተገደው ወጥተው ደቂቃ ባልፈጀ ጊዜ ውስጥ ሬሳቸው ብቻ ያገኙ በርካታ ናቸው። እንደወጡም መዳረሻቸው ያልታወቁ በልጅ ፍለጋ እህህ እንዳሉ ወደአለም ፍጻሜ የወረዱ እናቶችን ታሪክ ይቁጠራቸው። ይህ ክፉ ዘመን እራሱ ከፍቶ በእናቶቻችን ላይ ያሳደረው የአእምሮ ጠባሳ እስከ ሕልፈተ ሞታቸው ድረስ አብሯት ይዘልቃል። በኢሕአፓና በደርግ ፤በደርግና በሻቢያ ፤በደርግና በወያኔ ፤ በኦነግና በደርግ፤ ኦጋዴን ለመገንጠል እንታገላለን በሚሉትና በሌላው ሕብረተሰብ ብሎም በሶማሊያ ወረራ የኢትዮጵያ እናቶች ልጆቻቸውን በግራ በቀኝ አጥተዋል ። በተለይ እናቴ በነበረችበት የጎንደር ክፍለ ሀገር በተፈጸመ እርስ በእርስ ፍጅት ውስጥ በአካል ያየችውና ከባሏ/ከወላጅ አባቴ/ ጀምሮ ብዙ ያሳደገቻቸው ልጆች የደረሰባቸውን መከራና ሰቆቃ በአንድ ዘመን ደርግና ኢሕአፓ አሁን ወደመጨረሻው ደግሞ የወያኔና የደርግ ጦርነት እየተፈራረቁ በአካባቢው ያደረሱትን ችግር በአካል አይታዋለች፤ አልፋበታለች።ከዚያ ሁሉ መከራ ሽሽታ አዲስ አበባ ከእኛ ከቀሪ ከልጆቿ ጋር መቀመጥን መረጠች፤ በመካከል ደግሞ ወያኔዎች የበኩላቸውን የጥፋት ትልኮ ተሸክመው ወላጅ አባቴን ገለው ፤እየተግተለተሉ እስከነ ኮተታቸው አዲስ አበባ ደረሱ።

ይህን ሁሉ በአምሮዋ ተሸክማ እያለች ደግሞ እኔ በነበረኝ ፀረ-ወያኔ አቋም የተነሳ ወያኔ አሸናፊ እኔ የተሸናፊ ጎራ የተመደብንበት ወቅት በመድረሳችን በወያኔ እጅ ስወድቅና ወያኔዎች ከፊቷ በጥይት ደብድበው ሲገሉኝ በህሊናዋ በማየቷ ደም ለመትፋት ተገደደች። ምን ያድርግ ዘጠኝ ወር የተሸከመ ማህጸን እንደገና አማጠና ሌላ የልተጠበቀ ደም አመነጨ፤ የወላጅ አንጀት ሁኖባት እንጂ እርሷማ የሬሳ ሳጥኗ ተዘጋጅቶ የመሞቻ ቀኗን የምትቆጥርበት እድሜ ደረጃ ላይ መድረሷን በሚገባ ታውቀው ነበር ። አላስቻላት ያለው የልጅ ጉዳይ ሆኖባት ነው።ለመነሻየ ይህን ልግለጸው እንጂ በእኔና በቤተሰቤ ላይ የደረሰውን መከራ በስርአት ጊዜና ወቅት ሲፈቅድ ለሕዝብ ይፋ አደርገዋለሁ።በመሆኑም አሁን የቀነጨብኩት የቤተሰብ ታሪክ ለማነጻጸሪያ እንጂ የእኔን የግል ታሪክ ለመግለጽ ሳይሆን እናቶች ለልጆቻቸው ያላቸውን ሁለገብ ፍቅር በደስታና በመከራው የማይቀየር መሆኑንና በዛሬው መድረክ ላይ የምንነጋገረው ስለ እናት ብርቱካን፤ ስለዳኛ በርቱካን፤ ስለ ቃል ኪዳኗ ብርቱካን ስል ወጣት ብርቱካን፤ ስለፓርቲ ሊቀመንር ብርቱካን፤ ስል ሕዝብ ተመራጯ በርቱካን ሜደቅሳ በመሆኑ ነው።

አወ! እናት ለልጇ የዘጠኝ ወር ቤት ብቻ ሳትሆን የእድሜ ልክ ቤት ናት። የቋንቋችን መፍቻ እማማ ናት፡ የምግብ መጀመሪያችን እናት ናት፤ የፍቅር የሰብእና መገለጫችን "ሀሁ" እማማ ናት። የብሶታችን የደስታችን መግለጫ አሁንም አትጠገቧ እማማ ናት።ለሁሉም የሰው መሆኛችን ምንጭ እናት ናት። በእናት እጅ ያላደገ ልጅ ሰብእናው የተጓደለ ነው የሚባለውም ይህን ሁሉ የእናት ጸጋ ስለሚያጣ ነው። ታዲያ ዛሬ በዚህ የስብሰባ አዳራሽ የአመቱ ታላቅ ሰው ብለን የምናስባት እናት ብርቱካን ሕጻን ልጇን በግድ ተነጥላ በእስር ቤት ትገኛለች። የብርቱካንን የእናትነት ከልጇ መለየት በየቀኑ በየደቂቃው አስቡት ።ብርቱካን ከስራ ተመልሳ ቤት ስትገባ ሮጣ ሂዳ ልብሴ ጭቃ ነው እማማ የተከበረች ዳኛ ናት የሚል ቋንቋ ሳያስጨንቃት እንዳየቻት የምትጠመጠምባት ፤ እቅፍ አድርጋ እማይ የምትላት ጨቅላ ህጻን ልጇ ጥላና አደራውን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰታ ወደ እስር ቤት ወረደች። እስር ቤት እያለችም አብራት የምትጫወትበት  ጊዜና ሰአት  ይታወሳታል፤በአይነ ህሊናዋ ይመጣባታል እንግዲህ ይህ ትናንት በውን አለም የነበረ ዛሬ ለእርሷ ህልም የሆነ አለምን በእርሷ ቦታ ሁናችሁ አስታውሱት። ከልጅ መለየት ፈተና  ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ እኔ እራሴ በደርግ እስር ቤትም ሆነ በውያኔ ዘመን ታስሬ እና ተሰድጅ  ከምወዳቸው ልጆቹ ተለይቼ የቀመስኩት አንዱ ፈተና ነው "ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ " እንዲሉ አይደል። እዚህ ላይ ሁላችሁም በዚህ እለፉ የሚል ሰይጣናዊ ምኞት የለኝም ካለፈው ገጠመኝ ጋር በማጣመር ለመግለጽ ያሰብኩት መሆኑን ተገንዘቡልኝ። ለነገሩማ ያልታሰረና ያልተሰደደ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥሩ ትንሽ ነው መላው ሕዝባችን በአገሩ እስረኛ ሆኗል አይደል።

እራሷ ብርቱካን ያለችበት የስር ቤት አለም የሰቃይ መኖሪያ ቢሆንም በተለይ ሕጻኗን መለየት በእናትነት ቦታና አንጀት ውስጥ ሁናችሁ አስቡት የሚደርስባትን ችግርና መከራ የልጅ ናፍቆት ተጨምሮበት ባለፈው የመጀመሪያ እስሯ ወቅት የልጇን ናፍቆት በገለጸችበት ግጥሟ ውስጥ አንዱ ቃል"የእኔ ፍልቅልቋ" የሚል ነበር አወ የብርቱካን ፍልቅልቅ ዛሬ እንደገና ከእናቷ* ተነጥላለች ታዲያ የኢትዮጵያ እናቶች ምን እያደረጋችሁ ነው ያላችሁት? ቀሪው ሕብረተሰብስ የጣለችብንን አደራ እየተወጣን ነው? ወይስ አደራ በዮች ሁነናል ? በእውነቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንዱ የሚታወቅበት የጭዋነቱ መግለጫ አደራውን አክባሪ መሆኑ ነው። ታዲያ ይች እናት ለሀገር ደህንነት ሰላምና ፍቅር ብላ እስር ቤት ስትወርድ በየበኩላችን ምን አደረግን? አሁንም የተለመደውን ከንፈር መጠጣ ወይስ በጋራና በተቀነባበረ መልኩ ተደራጅተን እሷና መሰሎቿ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተምሳሌወችን ለማስፈታት እየታገልን ነው? አሁን ጥያቄአችን ብርቱካል ከታዳጊ ልጇ የምትለይበት ምንም አይነት የህግ ህጸጽ ስለአልፈጸመች በፖለቲካ አመለካከቷ የተነሳ ከመታሰሯ ተፈታ ሰላማዊ ትግሏን እንድትቀጥልና ከልጇ ጋር እንድትገናኝ ብሎም ብርቱካንን መሰል እናቶች ልጆቻቸውን ተንከባክበው እንዲያሳድጉ ከልጆቻቸው ጋር እንዲገናኙ የበኩላችን የይፈቱ ዘመቻችን ማጠናከር ይዋል ይደር የማይባል የአደራ ቃላችን ስለሆነ አደራችን አክባሪዎች መሆናችንን በተግባር ማሳየት ይኖርብና።

በርቱካን ፍትህ በናፈቀው ሕብረተሰብ ውስጥ የፍትህን ምንነት በአደባባይ በዋለችበት ችሎት ያሳያች ያስመሰከረች የሙያ ሰው በመሆኗ የሀገራችን የይስሙላ ችሎቶች ወደ ሕግ የበላይነትና የህግ አፈጻጸምን ስርአት ለናፈቀውና እንደበግ ግልገል ማንም ነፍጥ አንጋቢ እየጎተተ ከሚያንገላታውና ከሚያስርበት ኢ ፍታዊ አሰራር የምንላቀቅበትን መንገድ ያሳየችን የፍትህ ሰው በመሆኗ ፤ተምሳሌትነቷን ተከትለን ዜጎች እኩል በህግ ፊት የሚዳኙበት ስርአት እንዲመጣ በጋራ አሁንም እንታገል።

በሙያዋ የተነሳ የወያኔ አገዛዝ ሰለባ የሆነችውን ወጣቷን ዳኛ ብርቱካንንና በፍትህ እጦት ለመደበኛ እስር ቤት እንኳን በማይመጥኑ ጋጦች የታጎሩትን በእስር ሽህዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ከእስር እንዲፈቱ አሁንም በጋራ እንነሳ ለዚህም እውን መሆን የየበኩላችን ድርሻ እንወጣ ብርቱካን የአመቱ ሰው ስንል ብርቱካን የቆመችለት የታሰረችበትና እየታገለች ያለችው የፍትህ ስርአት እንዲሰፍን በመሆኑ ለሕግ የበላይነት መኖር በጋራ እንታገል።

ብርቱካን ገና ሩጣ ያልጠገበች በወጣትነት እድሜዋ ማከናወን የሚገባትን ስራ በውጥን ትታ በሙያዋ እንደብዙዎቹ ጊዜአዊ ምቾት ሳይስባት ሙያዋንና ጊዜዋን በሀገር ጉዳይ ላይ ያዋለች የአዲሱ ትውልድ ተመሳሌት በመሆኗ ሁላችንም ስለ መጭው ታሪክ ተረካቢ ትውልድ ስናወሳ ማየት ያለብን አሁን ምሳሌ የሆኑትን ብርቱካንንና መሰሎቿን ከጎናቸው ቁመን ካላበረታታንና የሚጓዙበትን ጎዳና መምራትና የተረካቢነት ደርሻቸውንም እሚወጡበትን መንገድ ተንከባክበን ይዘን ካላሳየን  ስለመጭው ማሰብ ብቻውን ቁም ነገር ላይ አይውልም።

ወጣቶችም እንደዚሁም ልትገነዘቡ የሚገባው ቁም ነገር ብርቱካንና መሰሎቿ ወጣቶች  እንደ ናንተ የተለያዩ የግል ሕይወት በዚህ እድሜአቸው መምራት ሲችሉ ነገር ግን ሀገርን አስቀድመው በግንባር ቀደም ለተሰለፉ ማገዝ ከጎናቸው በመሰለፍ ሁለገብ ተሳትፎና ድጋፍ ማሳየት አለባችሁ። ይህ ካልሆነ ግን በእነርሱ የደረሰው ችግር ወቀሪውም የወጣት ክፍል ስለሚዘልቅ ነግ በኔ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ያለፈን ትውልድ ወቃሽ ብቻ ሁናችሁ እንደምትቀሩና የሀገራችን መጭ እጣ እየከበደ እንዲያውም እራሱ ሀገር አለን ለማለትም ወደማያስደፍር ሂደት በማዘገም ላይ ስለሆን ይህንኑ ካሁኑ ተረድታችሁ ከመጥፋታችን በፊት ላለመጥፋት መነሳት ያለባችሁ ዘመን ላይ እንደምትገኙ ልትገነዘቡ ይገባል። ለማስፈራራት አይደለም  ባለፈው የኢትዮ - ኤርትራ ጦርነት ያጣናቸውን ወጣኞች ማስታወሱ ብቻ በቂ ይመስለኛል። ዛሬም ወያኔዎች የንቃተ ህሊና ደረጃቸው ገና የሆኑትን በርካታ  ወጣቶች  ለእኩይ አላማቸው አስፈጻሚ ያደረጉአቸውና አሁንም እየተጠቀሙባቸው መሆኑን ልብ ልንል ይገባል፤በመሆኑም የተሳሳቱትን መመለስ አንዱ የትግል ድርሻም ጭምር ነው።

ብርቱካን የሕዝብ ተመራጭ ናት። አንድ ሕዝብ የመረጠውን ወገን ደህንነት የማያስጠብቅና ለጥቃት አሳልፎ የሚሰጥ ከሆነ ሕዝብ በሕዝብነቱ መጠየቁ የማየቀር ነው ። በመሆኑም ብርቱካንንና ሌሎችንም የመረጣቸው ህዝብ ሊጠብቃት ይገባል ሊከላከልላት ይገባል። የወያኔ አገዛዝ በርቱካንና ሌሎችን በሰላማዊ መንገድ የታገሉትን ወገኖች ወስዶ እስር ቤት ሲያጉር እና የህዝብን አመጽ በኃይል ሲደመስስ የገጠሩ ሕዝብ አብሮ ከከተማው ጋር መተባበር ሲገባው ይህ አልሆነም።በዚህም የተነሳ ወያኔ እየነጠለ ሕዝብ ሲያግዝ  ለምን ብሎ በሆታ ወቶ የመከላከል እርምጃውን አላሳየም።የገጠሩ ህዝብ ከየመኖሪያ ቤቱ ሲፈናቀልና ሲገደል የከተማው ህዝብ አየጉድ! ብቻ ነው ተሸክሞ የሚቀመጠው፤ እዚህ ላይ አንድ የድሮ ተረት አስታዋሰኝ “የድሮ ሲራራ ነጋዴዎች በጉዞ ላይ እንዳሉ ይመሽባቸውና መንገድ ማደር ይገደዳሉ ከእነሱ አንዱ በጣም ፈሪ ስለነበር ከመሀላቸው እንዲያስተኙት ከመጠየቁ በተጨማሪ ዳውላ በላዩ ላይ እንዲጭነበት ያደርጋል፤ ይህም ሁኖ ተንኮለኛ ጅብ ከዚያ ሁሉ ነጋዴ እሱን ፈልጎ እግሩን መብላት ይጀምራል  በመሀል ሊሎቹ ነጋዴዎች ነቅተው ለመካለከል ማንን ነው? ማንን ነው? ብለው ሲጠይቁ ዝም በሉ የእኔን እግር ነው የሚበላው “አለ ይባላል እየሞትንም መሞታችን መከላከል ባለማቻላችን ወያኔ አሁን ከላይችን ላይ እንደ አውራ ደሮ ይጨፍርብናል። ይህ ሊዘገንነንና በቃን ሊያስብለን መቻል አለበት፤ ካለያ እንደ አሻንጉሊት እየከፋፈሉ ሲጫወቱብን ይኖራሉ።ህዝብ በጋራ በቃን ሊል

ይገባዋል። የፖለቲካ ሰዎች የሚባሉትም እርስ በእርስ መቧጨቃቸውን ትተው የአንዱ መጠቃት የሌላው መሆኑን ተገንዝበው እዚህ ላይ አያውቁትም ለማለት አይደለም ያውቁታል ግን በግል በፖለቲካ አውደ እለታቸው ታጥረው ማዶ ማየትን ስለተሳናቸውና ተባብረው እንደመነሳትና ልዩነትን በሚገባ አቻችሎ እንደመቆም በየኪሳቸው በያዙት የንጉሰ ነገስትነት አባዜ ብቻ ስለሚባክኑ ያች የኪስ ንግስና ከደብተር አልፋ ቁመንልህል የሚሉትን ህዝብ ሲያገለግል አልታየም። ይኽን ስል ብዙወቹ በተቃውሞ የሰላ ብእራቸውን ግን በተግባር የማይታይ ሙያቸውን እንደሚያሾሉ ይገባኛል።

ይህን ማድረግ ካልቻሉ ደግሞ የተለመደ ተከታዮቻቸውን የያዘው ቀላጤ እንደሚያስተላልፉ ይገባኛል። በዚህ ጉዞ ግን ግለሰቦች የጥቃቱ ሰለባ ከመሆን በመለስ ፓርቲዎቹ በሕዝብ እንዲፈሩ የአምባ ገነን በህሪያቸውን አጉልቶ ከማውጣት ውጭ ለሀገር የሚጠቅም ነገር አልታየም። እዚህ ላይ ስለቡድን አንድ ትንሽ ግጥም ላውገርግር፤

ወይ ቡድን
መቧደን በቡድን
አንድ ላይ መቧደን
በአንድ ላይ ሰው ማደን
በተራ ደግሞ መታደን
ወይ ቡድን
ወይ ቡድን
ወይ አድን
ወይ ታደን
ከሆነ ቁም ነገር
አንዱ አንዱን ማውገርገር
በፓርቲ መቧደን
በሃይማኖት ቡድን
በትውልድ መቧደን
በቋንቋም ተቧደን
በወንዝ በሸለቆ አንዱ አንዱን ማሳደን
ይህ የሚባል ቡድን በነትና ቡድን
ተመቶ ሲጎድል
ሌላው ተራ ቡድን ይላል ብቅ በድል
ተራውን ሊያጉላላ ተራውን ሊበድል
ቂም በቀል አንግቦ
በቂም በቀል ደቦ
አዲሱ ባሮጌው በሚቹ ላይ ሲስቅ
በጊዜው ሲሳለቅ
ከሞት የተረፈው በቁም ሲሸማቀቅ
ይህ ነው የቡድን ስንቅ
የቡድን ትንቅንቅ
የሚያስደርግ እንቅ


የሕግ ባለሙያው ዶ/ር ሸክስፒየር ፈይሳ ሽልማቱን ሲሰጡ

ምን አለ ቢቧደን ሰውስ ቢከራከር
በሃሳብ ደረጃ ቢሆንስ ፉክክር
ብሎስ ቢመካከር
ውጣ ውረድ አይደል የሰው ልጅ
ሕይወቱ
ማሸነፍ መሸነፍ መውደቅ መነሳቱ

በቡድን ተቧድኖ አገር ለመታደግ
ከታሰበ በደግ
ቸነፈር ሰቆቃን ካገር ለማስወገድ
የግፍ አገዛዝም ከምር እንዲወገድ
መቧደን ያሻናል ፍትህ እንዲጠበቅ
በጋራ ባንድ ላይ መቆም በተጠንቀቅ
ለመብት ለነፃነት
ለመቆም በህብረት

አሁን ያሻል ቡድን
በአንድ ላይ መቧደን
ቡድን ጥሩ ነብር ላሰበበትማ
ተመካክሮ ለእድገት በአንድ ብንስማማ
መስማማት ግድ ነው ወደድንም
ጠላንም
በፀብ መቀጠሉ ከቶ አላዋጣነም
እንቧደን አሁን በአንድነት ጎዳና
ይብቃን ሀገር ማፍረስ ለግል ብልጽግና

ታዲያ በየቡድኑ የተሰለፈው ወገን የአትንኩኝ ባይነቱ ወገንን ከማሸማቀቅ ተገቶ በጋራ መተራረም ላይ ቢያተኩሩና ከነደብተራው ደብዛ መጥፋት፤ ከነአበራ የማነአብ በወያኔ እስር ቤት ዘቅጦ መቅረት፤ ከነፕሮፌሰር አስራት በእስር ቤት ማቆ መሞት እስከ ብርቱካን መታሰር የታየን ችግር በጋራ ብንታገል ለውጤት እንደምንበቃና አሳሪውም የሕዝብ ፍራቻ እንዲያድርበት፤ የተቃዋሚወች የጋራ ክንድ ቢያርፍበት ምንኛ ባፈረና በፈራ፤ ከደዚህ አይነት የማን አለብኝ ተግባር በተገታ ነበር አገርንና ሕዝብን እንደአሻው አያምስም ነብረ፡አንድ ከሆን በጋራ ጉዳይ ላይ በአንድ ላይ ከቆምን  ስልጣን የወያኔ ሳይሆን የእኛ ነበር ግን ባለመተባበር አሳልፈን ሰጥተን ዛሬ ሰቶ አሳዳጅ ሆነን አረፍን።

በቅርቡ እንኳ ብርቱካን በትታሰረች ሰሞን አንዱ የፓርቲ ክንፍ ያሰራጨውን አሉባልታ የምናስታውሰው ጉዳይ ነው። አሁንም የፖለቲካው ሰዎችን የምናማርረው ፖለቲካኞች በመሆናችው ሳይሆን አካሄዳችሁን በተደጋጋሚ ፈትሻችሁ ሀገርን ለማዳን የሚያስችል ትርጉም ያለው ትብብር ቀይሱ።  ከዚያ ህዝቡን አይተባበረንም ይተባበራል የሚለውን ሀሳብ ለህዝብ አቅርቡ፡ በዚህ ረገድ የኢትዮጵ ሕዝብ ትብብር በኢሕአፓ የመጀመሪያ ዘመናት የታየውን ተሳትፎ ማስታወስ ይገባል። እንደዚሁም ፡ ትናትናም ቅንጅት ብቅ ባለበት ወቅት ይህንኑ አስመስክሯል። በእኔ እይታ መወዳደር መከራከር ጤናማ ከሆነ አይከፋም ለሕዝብና ለሀገር ካልጠቀመ ግን ጠንቅ ነውና አስቡበት፡ ሕዝቡም ማንን እንደሚከተል በማስገደድና በማስፈራራት ሳይሆን በራሱ ምርጫ እንድሚጓዝ የታየ እውነታ ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ጥሩ የሰራን ይደገፋል ያስፈራራን ይነቀፋል ድጋፍ ይነፍጋል ስለሆነም የህዝብ ድጋፍ ብቸኛ መለኪያው ተግባር ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ የጋራችን በመሆኗ የምንለውን ባይጥማችሁም ቢያንስ አዳምጡት ለሕዝብ በይፋ ባታወጡት እንኳ ቢያንስ በየድርጅቶቻችሁ ተነጋገሩበትና አንድ ደረጃ ላይ ድረሱ የቆማችሁት ሕዝብ ለመምራት ከሆነ ይዝብ የሚለውን ማዳማጥ ተገቢ ይመስለኛል። በአሁኑ ወቅት ብርቱካና መሰሎቿ የኢትዮጵያ ፖለቲካ መለኪያ ሚዛን፤ የብርቱ እናት ተምሳሌት፤የአዲሱ ትውልድ መስታዊት የሕዝብ ተመራጭነት አረአያ መሆናቸውን በመገንዘብ ሁሉም የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ፤የሰብአዊ መብት ተሚጋቾች፤ ሴቶች፤ ወጣቾች በጠቅላላም ህብረተሰቡ የብርቱካ የአመቱ ሰው መባል ወካይነቱ እሷን ብቻ አልመሆኑን ተገንዝበን  መጭው አመት የጋራ ትግል አመት እንዲሆን በጋር የምንነሳበት ዘመን መሆን አለበት የህዝብና የሀገር ችግር ሊያከትም የሚችልበት የአዲስ የትግል ዘመን እንዲሆን ጥሪ ከቫንኮቨር ካናዳ ይድረሳቹሁ!